የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Federal Attorney General

ቁጥር Ref.No 60/ጠ/ዐ/ህግ/ጊ/ፀ/
ቀን Date 16-06 2009

# ለፍትሕ ተከሳሽ

የፌ/ጠ/ዓ/መ/ቁ 249/09
የፌ/ፖ/ወ/መ/ቁ 472/09

**ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት**
**ልደታ ምድብ ወንጀል ችሎት**
**__አ/አበባ__**

**ከሣሽ...........የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ**

**ተከሣሾች......1ኛ/ ዶ/ር መረራ ጉዲና ጀፊ እድሜ 61**

አድራሻ፡-ኦሮሚያ ክልል፣ፊንፊኔ ዙሪያ ልዩ ዞን፣ቡራዩ ወረዳ፣

**2ኛ/ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ፣**

አድራሻ፡- በሌለበት

**3ኛ/ ጀዋር መሀመድ**

አድራሻ፡- በሌለበት

**4ኛ/ ኢሣት/የኢትዮጵያ ሣተላይት ቴሌቭዥን/ ፣**

አድራሻ፡- በሌለበት

**5ኛ/ ኦሮሞ ሚዲያ ኔትወርክ / O.M.N /**

አድራሻ፡- በሌለበት



Scanned by CamScanner

ቁጥር
Ref.No
ቀን
Date

## 1ኛ ክስ

### በ1ኛ፣በ2ኛ እና በ3ኛ ተከሳሾች ላይ

### ወንጀሉ

*በ1996 ዓ/ም የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/1/ሀ፣ለ፣38/1፣27/1፣238/1/ እና /2/ ሥር የተመለከተውን በመተላለፍ፣*

### የወንጀሉ ዝርዝር

ተከሣሾች በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን በቀጥታ እንዲሁም በመላ ሃሣባቸው በወንጀሉ ድርጊትና በሚሰጠው ውጤት ሙሉ ተካፋይ በመሆን፣የአድማ ስምምነት በማድረግ በፌደራል ወይም በክልል ህገ-መንግስት የተቋቋመውን ስርዓት በህገ-ወጥ መንገድ ለማፍረስ የፖለቲካ፣የሀይማኖታዊ ወይም የአይዲዮሎጂ አላማን ለማራመድ በማሰብ በመንግስት ላይ ተፅዕኖ በማሳደር ህብረተሰቡን ወይም የህብረተሰቡን ክፍል በማስፈራራት ወይም የሀገሪቱን መሰረታዊ ፖለቲካዊ ህገ-መንግስታዊ ኢኮኖሚያዊ ወይም ማህበራዊ ተቋማትን ለማናጋት እና ለማፍረስ እንዲሁም ሕገ-መንግስቱንና ሕገ-መንግስታዊ ሥርዓቱን በሀይል እናስወግዳለን በማለት በሚንቀሳቀሱት የአርበኞች ግንቦት ሰባት በማለት እራሱን በሚጠራው የሽብር ቡድን ተልዕኮ ለማሳካት በማሰብ የአርበኞች ግንቦት ሰባት የተባለው የሽብር ቡድን ከ2008 ዓ/ም ጀምሮ የሁከት እና ብጥብጥ ጥሪ በማስተላለፍ እንዲሁም በአንዳንድ ***የኦሮሚያ እና የአማራ ክልል*** አካባቢዎች ህብረተሰቡ ወደ ሁከት እንዲገባ በማድረግ በመቀስቀስና አመራር በመስጠት በተነሣው ሁከት ምክንያት በአማራ ክልል፣በደቡብና በሰሜን ጐንደር እና በባህርዳር ዙሪያ የመንግስትና መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት በኢንቨስትመንት በተሰማሩ ባለሀብቶች ንብረት



Scanned by CamScanner

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Federal Attorney General

ቁጥር ________
Ref.No
ቀን ________
Date

እንዲወድም፣መሠረተ ልማት እንዲቋረጥ፣ሰው እንዲሞት፣በሰው አካል ላይ ከባድና ቀላል ጉዳት እንዲደርስ በማድረግ፣ የአዲስ አበባ እና የፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን የጋራ ማስተር ፕላን ዕቅድ ለሁከት መቀስቀሻ በማድረግ ከ2006 ዓ/ም ጀምሮ በኦሮሚያ ክልል በተለያዩ ከተሞች ደጋፊዎቻቸውን ወደ ሁከት እንዲገቡ በማድረግ በዚህ ምክንያት መሠረተ ልማት እንዲቋረጥ መንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት ላይ ንብረት እንዲወድም ሰዎች እንዲሞቱ በሰው አካል ላይ ከባድና ቀላል ጉዳት እንዲደርስ በማስደረግ እንዲሁም መስከረም 24 ቀን 2009 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሸዋ ዞን ቢሾፍቱ ከተማ በተከበረው የኢሬቻ በዓል አከባበር ሥነ-ሥርዓት ላይ ሁከት አድራጊዎች በፈጠሩት ሁከት በሰዎች ላይ ሞት እንዲሁም በሰው አካል ላይ ከባድና ቀላል ጉዳት የደረሰ ሆኖ እያለ የመንግስት ታጣቂዎች በኦሮሞ ሕዝብ ላይ በወሰዱት ግድያ ተገድለዋል በማለት O.M.N /ኦሮሚያ ሚዲያ ኔትወርክ/ እና ኢሣት/ የኢትዮጵያ ሣተላይት ቴሌቪዥን/ ለተባለው የሽብር ቡድን ልሣን ለሆኑት የሁከት ጥሪ በማድረግ የሰዎች ሞት ምክንያት በመሆን እና መንግስታዊ እና መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት፣በኢንቨስትመንት የተሰማሩ ባለሀብቶች ንብረት እንዲወደም እርዳታ የጫኑ ተሽከርካሪዎች፣የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች እንዲቃጠሉ በማስደረግ አመራር በመስጠት የተሣፉ በመሆኑ የወንጀል ተሣትፏአቸው እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡



Scanned by CamScanner

ቁጥር
Ref.No
ቀን
Date

***1ኛ ተከሣሽ ዶ/ር መረራ ጉዲና፦*** የኦሮሞ ፌደራሊስት ኮንግረስ /ኦፌኮ/ የፖለቲካ ድርጅት አመራር በመሆን የፖለቲካ ድርጅቱን እንደሽፋን በመጠቀም የፖለቲካ፣የሀይማኖታዊ ወይም የአይዲዮሎጂ አላማን ለማራመድ በማሰብ በመንግስት ላይ ላይ ተፅዕኖ በማሳደር ህብረተሰቡን ወይም የህብረተሰቡን ክፍል በማስፈራራት ወይም የሀገሪቱን መሰረታዊ ፖለቲካዊ ህገ-መንግስታዊ ኢኮኖሚያዊ ወይም ማህበራዊ ተቋማትን ለማናጋት እና ለማፍረስ የአዲስ አበባ ከተማ እና የፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን የጋራ ማስተር ኘላን ተቃውሞን እንደ መነሻ በማድረግ ሁከትና ብጥብጥ እንዲቀጥል ቀን እና ወሩ ባልታወቀበት በ2006 ዓ/ም ኦፌኮ በተባለው የፖለቲካ ድርጅት የሥራ ክፍፍል በማድረግ በአንዳንድ የኦሮሚያ ከተሞች ደጋፊዎቻቸውን ወደ ሁከት እንዲገቡ በማድረግ በመንግስት እና በሕዝብ ተቋማት ፣መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማትና በኢንቨስትመንት በተሰማሩ ባለሀብት ንብረቶች ላይ ውድመት እንዲደርስ እንዲሁም በሰው አካል ላይ ከባድ የአካል ጉዳትና ሞት እንዲደርስ አስደርጓል፡፡

በአንዳንድ የኦሮሚያ ክልል ከተሞች ደጋፊዎቻቸውን ወደ ሁከት እንዲገቡ በማስደረግ በ2008 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሸዋ ዞን አምቦ አካባቢ የሚገኙ ኘሮጀክቶች የአምቦ ካራ የመንገድ ግንባታ በመቆራረጥ ካምፕ በማቃጠል በተሽከርካሪዎች እና ማሺነሪዎች ላይ ከብር 2,957,661.00 / ሁለት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ አምሳ ሰባት ሺ ስድስት መቶ ስልሳ አንድ ብር / በላይ የሚያወጣ ንብረት እንዲወድም አስደርጓል ፡፡

እንዲሁም በኦሮሚያ ክልል ቡራዩ ከተማ ከብር 42,598,204.98 / አርባ ሁለት ሚሊዮን አምስት መቶ ዘጠና ስምንት ሺ ሁለት መቶ አራት ብር ከዘጠና ስምንት ሳንቲም/ የሚያወጣ የተለያዩ ንብረቶች ላይ ጉዳት እና ውድመት እንዲደርስ በማስደረግ ፣ በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን



Scanned by CamScanner

ቁጥር
Ref.No
ቀን
Date

ወሊሶ፣አመያ፣ጎሮ፣ቶሌ፣ኢሉ፣ቀርሳ፣ወንጪ ወረዳዎች በቀበሌ መስተዳድር፣የግለሰብ መኖሪያ ቤቶች፣በኢንቨስትመንት ስራ የተሰማሩ የአበባ ድርጅቶች፣የአትክልት ማምረቻ የተለያዩ ንብረቶች ግምታቸው 17,352,482.00 / አስራ ሰባት ሚሊዮን ሦስት መቶ አምሳ ሁለት ሺ አራት መቶ ሰማንያ ሁለት ብር / በላይ የሆኑ ንብረት ላይ ጉዳት እንዲደረስ እና እንዲወድም አስደርጓል ፡፡

የኦነግ የሽብር ቡድን ልሣን ለሆነው የኦሮሚያ ሚዲያ ኔትወርክ /O.M.N/ ለተባለው ልሣን ሐምሌ 28 ቀን 2008 ዓ/ም ባስተላለፈው የሁከት ጥሪ ሐምሌ 30 ቀን 2008 ዓ/ም በመላው ኦሮሚያ ሕዝባዊ ተቋውሞ ለማካሄድ ታስቧል የሁከቱ ተካፋዮች እንዲሳተፉ በማለት የሁከት ጥሪ አስተላልፏል ፡፡

*መስከረም 24 ቀን 2009 ዓ/ም በኢሬቻ በዓል አከባበር ሥነ-ሥርዓት* ላይ የመንግስት ታጣቂዎች በኦሮሞ ህዝብ ላይ በወሰዱት ግድያ 678 ሰዎች ተገድለዋል በማለት በ/O.M.N/ የኦሮሞ ሚዲያ ኔትወርክ ቴሌቪዥን ጣቢያ የሁከት ጥሪ ካስተላለፈ በኋላ በአንዳንድ የኦሮሚያ ክልል ከተሞችና አካባቢዎች ሁከት እና ብጥብጥ እንዲነሣ ትግሉን እናስቀጥላለን በማለት ባደረገው የሁከት ጥሪ ከመስከረም 2009 ዓ/ም በኋላ የሠላማዊ ሰዎች ህይወት መጥፋት እና ከባድ የአካል ጉዳት መድረስ እንዲሁም በመንግስት እና መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት ላይ በኢንቨስትመንት በተሠማሩ ባለሀብቶች ንብረቶች ላይ እና የእርዳታ እህል በጫኑ ተሽከርካሪዎች ላይ ጥቃት እንዲደርስና እንዲወድም አስደርጓል፣በኦሮሚያ ክልል በኢሉአባቦራ፣ምዕራብ ሸዋ፣ምስራቅ ሸዋ፣ባሌ፣ሰበታ ከተማ፣ደቡብ ምዕራብ ሸዋ፣ አርሲ፣ምዕራብ አርሲ ዞን በመንግስት ንብረት *ላይ ብር 215,468,309.99* ሳንቲም/ ሁለት መቶ አስራ አምስት ሚሊዮን አራት መቶ ስድሳ ስምንት ሺህ ሶስት መቶ ዘጠኝ ብር ከዘጠና ዘጠኝ ሣንቲም/ በግል እና



Scanned by CamScanner

ቁጥር
Ref.No
ቀን
Date

መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት ንብረት ላይ *1,168,293,498.68 ብር/አንድ ቢሊዮን አንድ መቶ ስድሳ ስምንት ሚሊዮን ሁለት መቶ ዘጠና ሶስት ሺ አራት መቶ ዘጠና ስምንት ብር ከስድሳ ስምንት ሳንቲም* በላይ ግምቱ የሆነ ንብረት እንዲወድም አስደርጓል፡፡

ሁከትና ብጥብጡ ቀጥሏል በማለት በኦሮሚያ ክልል ውስጥ ከቡራዩ እስከ ደንቢዶሎ፣ጉጂ፣አምቦ፣ሱሉልታ፣ቦረና፣ቀርሳ፣ዶዶላ፣አርሲ፣አሳሳ፣አዳበርጋ ሁከቱ ተቀጣጥሏል በማለት *ለO.M.N/* ኦሮሞ ሚዲያ ኔትወርክ/ የሁከት ጥሪ አስተላልፏል ፡፡

***በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ*** ሸዋ ዞን በጀልዱ ወረዳ አምስት ቀበሌዎች ከሚገኙ የቀበሌ ታጣቂዎች የጦር መሣሪያ መውሰዳቸውን በ06/04/2008 ዓ/ም ከጀልዱ ከአንድ ግለሰብ ሲገለፅለት በሰላማዊ መንገድ ሽፋን ትግሉ እንዲቀጥል በማለት ተልዕኮ ሰጥቷል፣በተባበሩት አረብ ኢሜሬትስ የሚገኙት አንዳንድ የኦነግ ደጋፊዎች በሀገሪቱ ውስጥ ቁሮ የተባለው የኦነግ ሴል እያደረገ ያለውን ሁከት እና ብጥብጥ በገንዘብ ለመደገፍ የተሰበሰበውን ገንዘብ በኦፌኮ ፓርቲ የፋይናስ ኃላፊ በኩል እንዲላክ ፍቃደኝነቱን ገልፆል፡፡

***በተከሣሽ ኢሜይል*** ዲሴምበር 12 ኦሮሞ ከተባለው ደጋፊ በተላለፈለት የሁከት ጥሪ የአምቦ አካባቢ የኦነግ ሴል ወይም ቁሮ ያደረገውን ሁከትና አመፅ በኦሮሚያ ክልል በንብረት ላይ ጉዳት ደርሷል በማለት ጥሪ በማስተላለፍ፣3ኛ ተከሣሽ ግንቦት 17 ቀን 2007 ዓ/ም ለተከሣሽ ባስተላለፈው ጥሪ የተነሣውን ሁከትና ብጥብጥ በጣም ሠርታችኋል ሁከትና ብጥብጡ የአንድ ዘመቻ አካል ስለሆነ ሕዝባዊ ሁከቱን ለመሩት አመራሮች እና አስተባባሪዎች ክብር ይገባቸዋል ከተጠበቀው በላይ ውጤት አስገኝቷል በማለት ሁከቱን ከውስጥና ከውጭ ካሉ ከግብረአበሮቹ ጋር በመምራት ህገ- መንግስቱን እና ህገ -መንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለማስወገድ በመንቀሳቀስ ተሳታፊ ሆኗል ፡፡



Scanned by CamScanner

ቁጥር
Ref.No
ቀን
Date

***2ኛ ተከሣሽ ፐ/ር ብርሃኑ ነጋ፦*** የአርበኞች ግንቦት ሰባት ብሎ እራሱን የሚጠራው የሽብርተኛ ቡድን አመራር በመሆን የፖለቲካ፣የሀይማኖታዊ ወይም የአይዲዮሎጂ አላማን ለማራመድ በማሰብ በመንግስት ላይ ላይ ተፅዕኖ በማሳደር ህብረተሰቡን ወይም የህብረተሰቡን ክፍል በማስፈራራት ወይም የሀገሪቱን መሰረታዊ ፖለቲካዊ ህገ-መንግስታዊ ኢኮኖሚያዊ ወይም ማህበራዊ ተቋማትን ለማናጋት እና ለማፍረስ እንዲሁም ሕገ-መንግስቱንና ሕገ-መንግስታዊ ሥርዓቱን በሀይል ለማስወገድ ዓላማና ተልዕኮ በመያዝ በውጭ ሀገር ሆኖ በመንቀሳቀስ የሽብር ቡድኑን አባላት የሽብር ተልዕኮ በመስጠት ከ2006 ዓ/ም ጀምሮ በአማራ ክልል በአንዳንድ አካባቢዎች በሕቡዕ አባላትን በማስመልመል እና እንዲንቀሳቀሱ በማድረግ ሁከቱ እንዲቀጥል በማለት የሽብር ቡድኑ ልሣን በሆነው ኢሣት /የኢትዮጵያ ሣተላይት ቴሌቪዥን/ በተለያየ ቀን 2009 ዓ/ም የሁከት ጥሪ በማድረግ ከእንግዲህ የኢትዮጵያ አርሶ አደር ግብርና የማዳበሪያ ዕዳ አይከፍልም በማለት አርሶ አደሩ በመንግስት ላይ እንዲያምፅና ለፍትህ ስርአቱ እንዳይገዛ ለዳኝነት በየአካባቢው ፍርድ ቤት አይሄድም በማለት የሁከት ጥሪ አስተላልፏል ::

እራሱን የአርበኞች ግንቦት ሰባት ብሎ በሚጠራው የሽብር ቡድን ዓላማ ከግብ ለማድረስ እኔም ሆነ ድርጅቱ አርበኞች ግንቦት ሰባት እስከ መጨረሻው የደም ጠብታ ድረስ የምንታገል መሆኑን ቃላችንን እንሰጣለን በማለት መንግስትን በሰላማዊ መንገድ መታገል ሞኝነት ነው፣ በሀይል መታገል አለብን በሰሜኑ የአገራችን ክፍል የሚገኘውን ሕዝባችን መሣሪያውን እየወለወለ ወደ በረሀ እየገባ ነው ይህ የህዝብ አመፅ በተደራጀ መልኩ እንዲቀጥል እና የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ አቅርቦት ወደፊትም እናደርጋለን የዚህ ዓይነት ትጥቅ ትግል በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል



Scanned by CamScanner

ብቻ ሣይሆን በመላው ኢትዮጵያም እንዲስፋፋ እየሠራንበት እንገኛለን በየአካባቢው የተመሠረቱ የሕዝባዊ እምቢተኝነት አስተባባሪ ኮሚቴዎች የትግል ስልት በመንደፍ በመንግስት ተቋማት የልማት አውታሮች እና የመገናኛ መዋቅሮች የገንዘብ ምንጮች በመንግስት የኢኮኖሚ ኢላማዎች ላይ ማነጣጠር ያለበት መሆኑን፣የጋራ ሽግግር መንግስት በአስቸኳይ ተዘጋጅቶ በአገሪቱ በግድ አመፅ እውን ይሆናል እንዲሁም ሳዲቅ አህመድ ከተባለው *B.B.N* ከተባለ የሽብር ቡድን ሚዲያ ጋር አርበኞች ግንቦት ሰባት እያደረገ ያለው ትግል በኤርትራ በረሀ ብቻ የተወሰነ ሣይሆን ሕዝባዊ እምቢተኝነት መሆኑን ኤርትራ ያለውን የሽብር ቡድኑን መገናኛ አደረጃጀት በቅርብ እንደሚያደራጅ እና የትጥቅ ትግልም እንደሚቀጥል የሽብር የሁከትና የብጥብጥ ጥሪ አስተላልፏል።

በ06/01/2009 ዓ/ም አባ ዘወልድ ለተባለ በሽብር ቡድኑ ስር ለሚንቀሳቀሰው አባል የሚያስፈልጋቸውን ነገር ከአርበኞች ግንቦት ሰባት አመራር ከሆነው በአስማረ ብሩ አማካይነት እንደሚላክላቸው የገለፀ ሲሆን በ12/01/2009 ዓ/ም ሳጅን አገኘሁ ለተባለ የሽብር ቡዱኑ የሴል አባል ሁለት ሺህ ጥይት እንዲሁም ስንቅ እና የጦር መሳሪያ እንደሚላክላቸው ገልፆለታል፣በመንግስት ላይ ጦርነት በመክፈት የሚያሸንፉበትን አቅጣጫ መቀየሱን ማሰልጠኛ ማዕከል እንዲከፍቱ ተልዕኮ ሰጥቷል።

*በ16/01/2009 ዓ/ም በ15/01/2009 ዓ/ም፣በ13/02/2009 ዓ/ም፣በ15/03/2009 ዓ/ም፣በ16/03/2009 ዓ/ም ፣በ17/03/2009 ዓ/ም በ03/04/2009 ዓ/ም* በተለያየ ጊዜ በሀገር ውስጥ በህዕቡ የሚንቀሳቀሱትን የሴል አባላት ተበታትነው ከሚንቀሳቀሱ በአንድነት ሁነው በተሰማሩበት አካባቢ ጥቃት እንዲያደርሱ፣ከኤርትራ የገቡ እና የሚገቡ የሽብር ቡድን አባላት



Scanned by CamScanner

ያሉ በመሆኑ ሁከቱ እና ብጥብጡ መቀጠል ያለበት መሆኑን በመግለፅ ህገ- መንግስቱን እና ህገ -መንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለማስወገድ በመንቀሳቀስ ተሳታፊ ሆኗል ::

***3ኛ ተከሣሽ ጀዋር መሃመድ*** በሚኖርበት ውጭ ሀገር የኦነግ የሽብር ቡድን አመራር በመሆን የሽብር ቡድኑን ተልዕኮ ለመፈፀም፣የፖለቲካ፣የሀይማኖታዊ ወይም የአይዲዮሎጂ አላማን ለማራመድ በማሰብ በመንግስት ላይ ተፅዕኖ በማሳደር ህብረተሰቡን ወይም የህብረተሰቡን ክፍል በማስፈራራት ወይም የሀገሪቱን መሰረታዊ ፖለቲካዊ ህገ-መንግስታዊ ኢኮኖሚያዊ ወይም ማህበራዊ ተቋማትን ለማናጋት እና ለማፍረስ እንዲሁም ሕገመንግስቱንና ሕገ-መንግስታዊ ሥርዓቱን በሀይል ለማስወገድ በማሰብ የአዲስ አበባ ከተማ እና የፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን የጋራ ማስተር ፕላን ዕቅድ ለሁከት መቀስቀሻ በማድረግ ለሽብር ቡድኑ አመራር በመስጠት የብጥብጥና የሁከት ጥሪ በማስተላለፍ በኦሮሚያ ክልል በአንዳንድ አካባቢዎች ተከስቶ የነበረውን ሁከትና ብጥብጥ */O.M.N/* የኦሮሞ ሚዲያ ኔትወርክ በተባለው የሽብር ቡድኑ ልሣን በመጠቀም ሁከትና ብጥብጡ እንዲቀጥል አመራር በመስጠት፣በ05/01/2009 ዓ/ም ከወቅታዊ ሁኔታ ጋር ተያይዞ ነጋዴዎች ለሕብረተሰቡ የሚያቀርቡትን የተለያዩ የንግድ ቁሳቁሶች እንዳይሸጡ፣እንዳያቀርቡ፣እንዳይገዙ እንዲሁም የትራንስፖርት አቅርቦት እንዳይኖር የተደረገው አስበንበት ነው ምክንያቱም ይህ የመንግስትን ገቢ ከሚያዳክሙ አንዱ እስትራቴጂያዊ እቅዳችን ነው በማለት የሁከት ጥሪ መግለጫ አስተላልፏል።

በኦሮሚያ ክልል ውስጥ በተለያዩ ከተሞች ተደረጎ የነበረው ሁከትና ብጥብጥ ውጤታማ እንደሆነ ምክንያቱም ከ200 በላይ በሚገኙ ከተሞች እና ወረዳዎች ላይ በተለያየ ቦታዎች



Scanned by CamScanner

በተመሣሣይ ቀን እና ሠዓት በርካታ ተቃውሞዎች እንደተደረጉ፣በተለያዩ የኦሮሚያ ከተሞች የልማት ገቢዎች ለመንግስት የማያስገቡ ከሆነ መንግስትን ማዳከም ይቻላል እንዲሁም ኢንቨስትመንትን ማዳከም ይቻላል በማለት በአንዳንድ የኦሮሚያ ከተሞች ደጋፊዎቹን ወደ ሁከት እንዲገቡ በማስደረግ በ2008 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሸዋ ዞን አምቦ አካባቢ የሚገኙ ፕሮጀክቶች የአምቦ ካራ የመንገድ ግንባታ በመቆራረጥ ካምፕ በማቃጠል በተሽከርካሪዎች እና ማሽነሪዎች ላይ ብር 2,957,661.00 / ሁለት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ አምሳ ሰባት ሺህ ስድስት መቶ ስድሳ አንድ ብር / በላይ የሚያወጣ ንብረት እንዲወድም አስደርጓል ። እንዲሁም በኦሮሚያ ክልል ቡራዩ ከተማ ብር 42,598,204.98 / አርባ ሁለት ሚሊዮን አምስት መቶ ዘጠና ስምንት ሺህ ሁለት መቶ አራት ብር ከዘጠና ስምንት ሳንቲም/ በላይ የሚያወጣ የተለያዩ ንብረቶች ጉዳት እና ውድመት እንዲደርስ በማስደረግ ። በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ወሊሶ፣አመያ፣ጎሮ፣ቶሌ፣ኢሉ፣ቀርሳ፣ወንጪ ወረዳዎች በቀበሌ መስተዳድር፣የግለሰብ መኖሪያ ቤቶች፣በኢንቨስትመንት ስራ የተሰማሩ የአበባ ድርጅቶች፣የአትክልት ማምረቻ የተለያዩ ንብረቶች እና በመንግስት ተቋማት ግምታቸው ብር 17,352,482.00/ አስራ ሰባት ሚሊዮን ሦስት መቶ አምሳ ሁለት ሺህ አራት መቶ ሰማንያ ሁለት ብር/ በላይ የሆነ ንብረት ላይ ጉዳት እንዲደረስ እና እንዲወድም አስደርጓል ።

የእኛ ሕዝብና የኦነግ ቄሮዎች ከመንግስት የፀጥታ ኃይሎች የጦር መሣሪያ እየነጠቁ እራሣቸው በመታጠቅ ትግሉን ማስቀጠል እንዳለባቸው፣በምዕራብ ሸዋ እና አርሲ አካባቢ ከመንግስት ታጣቂዎች ላይ የጦር መሣሪያ እየተቀማ መሆኑን፣ከመስከረም 2009 ዓ/ም ጀምሮ ***በኦሮሚያ ክልል በኢሉአባቦራ ዞን፣በምዕራብ ሸዋ፣ምስራቅ ሸዋ፣ምስራቅ ወለጋ፣ባሌ፣ሰበታ ከተማ፣ደቡብ ምዕራብ ሸዋ፣አርሲ፣ምዕራብ አርሲ ዞኖች*** በተደረገው ሁከትና ብጥብጥ በመንግስት ንብረት ላይ



Scanned by CamScanner

ግምቱ ከብር 215,468,309.99 / ሁለት መቶ አስራ አምስት ሚሊየን አራት መቶ ስልሳ ስምንት ሺህ ሶስት መቶ ዘጠኝ ብር ከዘጠና ዘጠኝ ሣንቲም/ ፣ በግል እና መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት ንብረት ላይ ብር 1,168,293,498.68 /አንድ ቢሊየን አንድ መቶ ስድሳ ስምንት ሚሊየን ሁለት መቶ ዘጠና ሶስት ሺ አራት መቶ ዘጠና ስምንት ብር ከስድሳ ስምንት ሳንቲም/ በላይ ግምት የሆነ ንብረት እንዲወድም አስደርጓል፡፡

በ24/01/09 ዓ.ም ለO.M.N ኦሮሚያ ሚዲያ ኔትወርክ በኢሬቻ በዓል ላይ መንግስት አንድም ጥይት አልተኮሰም የሚለው ውሸት ነው 175 ሰዎች ተገድለዋል፡፡ 678 ሰዎች ሞተዋል በማለት የሁከት እና የብጥብጥ ቅስቀሣ በማድረግ ጥሪ በማስተላለፍ ህገ- መንግስቱን እና ህገ -መንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለማስወገድ በመንቀሳቀስ ተሳታፊ ሆኗል ፡፡

በአጠቃላይ ተከሣሾች የአድማ ስምምነት በማድረግ ሽብር እና ሁከት በሀገር ውስጥ እንዲቀጥል፣መንግስታዊ እና መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት ንብረት እንዲወድም ሕገ-መንግስቱንና ሕገ-መንግስታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለማስወገድ ሁከትና ብጥብጥ እንዲፈጠር በተፈጠረው ሁከትና ብጥብጥ አመራር በመስጠት የተሣተፉ በመሆኑ በዋና ወንጀል አድራጊነት በፈፀሙት በሕገ-መንግስቱና ሕገ-መንግስታዊውን ስርዓት በሃይል ለማስወገድ ሙከራ ወንጀል ተከሰዋል፡፡



Scanned by CamScanner

ቁጥር
Ref.No
ቀን
Date

## 2ኛ ክስ

## በ4ኛ እና በ5ኛ ተከሣሾች ላይ

## ወንጀሉ

*በ1996 ዓ/ም የወጣውን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/1/ሀ ለ እና 38፣34/1/እና የፀረ-ሽብርተኛነት አዋጅ ቁጥር 652/01 አንቀጽ 5/1/ለ ሥር የተመለከተውን በመተላለፍ፣*

## የወንጀሉ ዝርዝር

ተከሣሾች በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን ወንጀሉና ወንጀሉ የሚሰጠውን ውጤት በመቀበል የአድማ ስምምነት በማድረግ መንግስት የሚለወጠው ሕገ-መንግስታዊ በሆነ መርህ በምርጫ ብቻ ሆኖ እያለ ኢ-ሕገመንግስታዊ በሆነ መንገድ በሁከትና በብጥብጥ ህገ-መንግስቱን እና ህገ-መንግስታዊ ሥርዓቱን በሀይል አስወግዳለሁ በማለት በሚንቀሳቀሰው *እራሱን የአርበኞች ግንቦት ሰባት የሽብር ቡድን እና እራሱን የኦሮሞ ነጻነት ግንባር /ኦ.ነ.ግ/* በማለት በሚጠራው የሽብር ቡድኖች መሆናቸውን እያወቁ ለሽብር ቡድኖቹ ልሣን በመሆን በአገሪቱ ውስጥ በአንዳንድ አካባቢዎች የነበረውን የሁከትና ብጥብጥ ለሰው ህይወት መጥፋትና ንብረት በማውደም ለተሣተፉት የሁከት ተካፋዮች የሽብር ቡድን ፈጻሚዎችንና አስፈጻሚዎች ሁከቱ እንዲቀጥል 1ኛ፣ 2ኛ እና 3ኛ ተከሣሾች ሕገ-መንግስቱንና ሕገ-መንግስታዊ ሥርዓቱን በሁከትና በብጥብጥ እናስወግዳለን በማለት የሚያስተላልፉትን ጥሪ ልሣን በመሆን በማስተላለፍ ድጋፍ አድርገዋል።



Scanned by CamScanner

ቁጥር
Ref.No
ቀን
Date

***4ኛ ተከሣሽ ኢሣት ወይም የኢትዮጵያ ሣተላይት ቴሌቭዥን*** የአርበኞች ግንቦት ሰባት የሽብር ቡድንና አመራር ለሆነው ለ2ኛ ተከሣሽ የሚዲያ ሽፋን በመስጠት ተከሣሹ ያስተላለፈውን የሁከት ጥሪ ማለትም መስከረም 22 ቀን 2009 ዓ/ም በእሬቻ በዓል አከባበር ላይ የመንግስት ወታደሮች በወሰዱት እርምጃ ለሞቱት ወገኖች በጐንደርና አካባቢው ለነፃነት ሲታገሉ የተሰው ወገኖች እንዳሉ ዓላማቸውን ከግብ ለማድረስ እኔም ሆነ ድርጅቴ የአርበኞች ግንቦት ሰባት እስከ መጨረሻው የደም ጠብታ ድረስ የምንታገል መሆኑን ቃላችንን እንሰጣለን በማለት ያስተላለፈውን የሁከት እና የሽብር ጥሪ በማስተላለፍ፣

መንግስትን ለመጣል በሰላማዊ መንገድ መታገል ሞኝነት እንደሆነ እና በሀይል መታገል እንዳለብን ይህንንም ለማድረግ በአሁን ሰዓት በሰሜኑ የአገራችን ክፍል የሚገኘው ህዝባችን መሣሪያውን እየወለወለ ወደ በረሀ እየገባ ነው ሁከቱ በተደራጀ መልኩ እንዲቀጥል እና ለትግሉ የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ እያደረግን እንደሆነ ወደፊትም እንደምናደርግ እንድታውቁ እፈልጋለሁ፣የዚህ አይነት ትጥቅ ትግል በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ብቻ ሣይሆን በመላው ኢትዮጵያ እንዲስፋፋ እየሠራንበት እንገኛለን በማለት የሽብር ጥሪ ያስተላለፈ በመሆኑ፣

ትግሉ ብዙ የሰው ሕይወት ሣያስከፍል ከዳር እንዲደርስ በመንግስት ሥር ተጠርንፎ የመከላከያ ሠራዊት ከመንግስት ጎን ሣይሆን ከሕዝብ ጐን እንዲቆም የምናደርገው እንቅስቃሴ አሁንም ተጠናክሮ ይቀጥላል፣በየአካባቢው የተመሠረቱ የህዝባዊ እምቢተኝነት አስተባባሪ ኮሚቴዎች ለየአካባቢዎች የሚሆን የትግል ስልት በመንደፍ በመንግስት ንብረቶች እና የመገናኛ መዋቅሮች የገንዘብ ምንጮች እና በአጠቃላይ ስርአቱ የኢኮኖሚ እና የሥነ-ልቦና ጫና በሚፈጥሩ ኢላማዎች ላይ ማነጣጠር አለበት በማለት ያስተላለፈውን የሁከት ጥሪ በማስተላለፍ፣***ለ1ኛ***



Scanned by CamScanner

ቁጥር
Ref.No
ቀን
Date

ተከሣሽ በሰጠው የሚዲያ ሽፋን ሰኔ 01 ቀን 2008 ዓ/ም መንግስት ወደም ሆነ ተገዶ የሚያስብበት፣አስገድደንም ለመደራደር የምንችልበት መንገድ እንዲፈጠር ኢሣት ቴሌቭዥን ትብብር እንዲያደርግ ጥሪ አስተላልፏል፣

ሕዳር 25 ቀን 2008 ዓ/ም ተማሪዎች ላይ ያልተመጣጠነ የኃይል እርምጃ በብዙ ቦታዎች ተወስዷል፣ያልታጠቀ ተማሪ ባዶ እጁን የሚሄዱ ተማሪ መደብደብና ማሠር በስፋት ቀጥሎበታል በማለት ያስተላለፈውን የቅስቀሣና የሁከት ጥሪ አስተላልፏል።

ሰኔ 01 ቀን 2008 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል በተቀጣጠለው አመፅ በኦሮሚያ ዞን ባለስልጣናት ወጣቶች አነግን እያወደሱ ድንጋይ እየተሸከሙ መንገድ እየዘጉ ነው በማለት የሁከት ጥሪ አስተላልፏል።

***5ኛ ተከሣሽ /O.M.N/ የኦሮሞ ሚዲያ ኔትወርክ*** በማለት እራሱን የሚጠራው ውጭ ሀገር የሚገኘው ሚዲያ 1ኛ ተከሣሽ ጥቅምት 28 ቀን 2008 ዓ/ም የሁከት እና የአመፅ ጥሪ ሲያስተላልፍ ሚያዝያ 22 ቀን የሀዘን መታሰቢያ ሆኖ በየአመቱ እንዲከበር ፖርቲው ወስኗል በማለት ያስተላለፈውን የሁከት ጥሪ በማስተላለፍ እንዲሁም ሕዝባዊ ተቃውሞ ሐምሌ 30 ቀን 2008 ዓ/ም በመላው ኦሮሚያ ለማካሄድ ታስቦ በዝግጅት ላይ ለሚገኘው ለመላው ኦሮሚያ ተቃውሞ ተሣታፊዎች በተቃውሞው ላይ እንዲሣተፉ በማለት ማስተላለፉን መስከረም 24 ቀን 2009 ዓ/ም በእሬቻ በዓል አከባበር ሥነ-ሥርዓት ላይ የመንግስት ታጣቂዎች በኦሮሞ ሕዝብ ላይ በወሰዱት ግድያ እስከ አሁን ድረስ *678 ሰዎች* ተገድለዋል በማለት የሽግግር መንግስት በአስቸኳይ በማቋቋም ከአሁን በኋላ መንግስት ሕዝቡን ማስተዳደር አይችልም በኦሮሚያ ክልል ውስጥ ያለው ማለትም ከቡራዩ እስከ ደንቢዶሎ ጉጂ አምቦ፣ሆለታ፣



Scanned by CamScanner

ቁጥር
Ref.No
ቀን
Date

በረና፣ቀርሳ፣ዶዶላ፣አርሲ፣አዳበርጋ፣አሳሳ፣አካባቢዎች ሁከት እና ብጥብጥ ይቀጥላል የሽግግር መንግስት ካልተቋቋመ እየተፈፀመ ያለው ግድያ ይቀጥላል በማለት የ1ኛ ተከሣሽን የሁከት እና ብጥብጥ ጥሪ አስተላልፏል፡፡

በ5/01/09 ዓ/ም ከወቅታዊ ሁኔታ ጋር ተያይዞ ነጋዴዎች ለህብረተሰቡ የሚያቀርቡትን አቅርቦት እንዲሁም በ29/11/08 3ኛ ተከሣሽ ያደረገውን የሁከት ጥሪ በ30/11/08 ዓ/ም በሚደረገው ሕዝባዊ ተቃውሞ የሀይል እርምጃ የሚወሰድ ከሆነ የጀመራችሁትን የውስጥ ለውስጥ መደራጀት በማጠናከር አስፈላጊ የሆነ እና መንግስትን ማስወገድ የሚችል እርምጃ መውሰድ አለባችሁ በማለት ያስተላለፈውን የሁከትና ብጥብጥ ጥሪ አስተላልፏል፡፡

በ02/12/08 ዓ/ም በመንግስት ባለስልጣናት ላይ ልዩ እርምጃ እንዲወሰድ ከኦሮሚያ ሚሊሻ ጦር መሣሪያ ተፈቶ አጋጣሚውን በመጠቀም የጦር መሣሪያዎች በእጃቸው ያስገቡ የጦር መሣሪያ በማቅረብ ረገድ ጥረት ይደረግ፣የተለያየ የንግድ ቁሳቁሶች እንዳይሸጡ እንዳያቀርቡ እንዲሁም የትራንስፖርት አቅርቦት እንዳይኖር የተደረገው አስበንበት ነው ምክንያቱም ይህ የመንግስትን ገቢ ከሚያዳክሙ አንዱ ስትራቴጂ ነው በማለት በO.M.N /የኦሮሞ ሚዲያ ኔትወርክ/ 3ኛ ተከሣሽ የሰጠውን የሁከትና ብጥብጥ በማስተላለፍ፣

በእሬቻ በአል አከባበር ሥነ-ስርዓት ላይ መንግስት 175 ሰዎች በጥይት ገድሏል 678 ሰዎች ሞተዋል መንግስት የግድያ እርምጃ መውሰድ የቻለው የመንግስት ካቢኔዎች እና የሚፈልጋቸው ሰዎች በመድረክ ላይ እንዳይናገሩ ስለተደረገ ነው በማለት በ24/01/09 ዓ/ም የሁከት እና ብጥብጥ ጥሪ በማስተላለፍ ፣



Scanned by CamScanner

ቁጥር
Ref.No
ቀን
Date

በኦሮሚያ ክልል ውስጥ በአንዳንድ አካባቢዎች ተደርጎ የነበረው ሁከትና ብጥብጥ ውጤታማ እንደሆነ ምክንያቱም ከ200 በላይ በሚገኙ ከተሞች እና ብዙ ወረዳዎች ላይ በተለያየ ቦታዎች በተመሣሣይ ቀንና ሠዓት በርካታ ተቃውሞዎች እንዲደረጉ፣

በተለያዩ የኦሮሚያ ከተሞች ለመንግስት የልማት ገቢዎችን የማያስገቡ ከሆነ መንግስትን ማዳከም ይቻላል ኢንቨስትመንትንም ማዳከም ይቻላል የእኛ ሕዝብና ቄሮዎች ከመንግስት የፀጥታ ሀይሎች መሣሪያ እየነጠቁ ለራሣቸው በመታጠቅ ትግሉን ማስቀጠል አለብን በምዕራብ ሸዋ እና በአርሲ አካባቢ ሁከትና ብጥብጡ እንዲቀጥል ያስተላለፈውን የሁከት ጥሪ በሚዲያው ተከሣሽ ልሣን በመሆን ድጋፍ የሰጠ በመሆኑ፣

በ05/01/09 ባደረገው ቃለ ምልልስ በኦሮሚያ በተደረገው አድማ የአድማውን አዋጅ ባልተቀበሉ ሰዎች ላይ እርምጃ መውሰዱን ኢኮኖሚውን ማዳከም፣የንግድ እንቅስቃሴዎች ላይ እርምጃ መወሰዱን፣ኢኮኖሚውን በማዳከም የንግድ እንቅስቃሴ እንዲዳከም አድርገናል በማለት የሰጠውን የሁከት መግለጫ በማስተላለፍ ተሣትፏል።

በአጠቃላይ ተከሣሾች የኦነግና የአርበኞች ግንቦት ሰባት የሽብር ቡድን ልሣን በመሆን ሚድያን እና ሙያን ሽፋን በማድረግ 1ኛ፣2ኛ እና 3ኛ ተከሣሾች የሚያስተላልፉትን የሁከትና የብጥብጥ ጥሪ በመቀበል በሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት በሽብርተኝነት ለተፈረጁት እራሱን የኦሮሞ ነጻነት ግንባር በማለት ለሚጠራው የሽብር ቡድን እና የአርበኞች ግንቦት ሰባት የሽብር ቡድን ድጋፍ በመስጠት በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን ለሽብርተኛ ቡድን ድጋፍ መስጠት ወንጀል ተከሰዋል።



Scanned by CamScanner

## 3ኛ ክስ

### በ1ኛ ተከሣሽ ላይ

### ወንጀሉ

*በሚኒስትሮች ምክር ቤት የወጣውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር 01/2009 ዓ/ም አንቀጽ 12/1 ሥር የተመለከተውን እና በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ኮማንድ ፖስት የወጣውን የአስቸኳይ ጊዜ እርምጃ አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 2/1 ሥር የተመለከተውን በመተላለፍ፣*

### የወንጀሉ ዝርዝር

ሕገ-መንግስታዊ ሥርዓቱን ለማስከበር የሚኒስትሮች ምክር ቤት መስከረም 28 ቀን 2009 ዓ/ም የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በመደንገግ በአስቸኳይ ጊዜ እርምጃ አፈጻጸም መመሪያ ከሽብርተኛ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት በማድረግ በሽብር ከተሰየሙ ድርጅቶች ግንኙነት ማድረግ የተከለከለ መሆኑን ተከሣሽ እያወቀ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሽብርተኝነት በተፈረጀው እራሱን የአርበኞች ግንቦት ሰባት ብሎ በሚጠራው የሽብር ቡድን ሊቀመንበር ከሆነው 2ኛ ተከሣሽ ፕ/ር ብርሃኑ ነጋ ጋር በመሆን በ02/03/09 ዓ/ም ቤልጅየም ሀገር ውስጥ በመገናኘት እንዲሁም ከO.M.N የኦሮሞ ሚዲያ ኔትወርክ ከተባለው የ5ኛ ተከሣሽ ድርጅት ሠራተኞች የኦነግ የሽብር ቡድን አባላትና ደጋፊዎች ባዘጋጁት የስብሰባ መድረክ በመገናኘት ባደረገው ንግግር ኦሮሚያ ውስጥ አንዳንድ አካባቢዎች ለተፈፀመው ሁከትና ብጥብጥ ድጋፉን የገለፀ በመሆኑ በፈፀመው የአስቸኳይ ጊዜ እርምጃዎች ጋር የተያያዙ ግዴታዎችን መተላለፍ ወንጀል ተከሷል።



Scanned by CamScanner

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Federal Attorney General

ቁጥር ____________
Ref.No
ቀን ____________
Date

## 4ኛ ክስ

### በ1ኛ ተከሣሽ ላይ

### ወንጀሉ

በ1996 ዓ/ም የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀጽ *486/ለ/* ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ፣

### የወንጀሉ ዝርዝር

ተከሣሽ ጥርጣሬን የሚፈጥር የሀሰት ወሬ ለማውራት በማሰብ የኢትዮጵያና የናይጀሪያ ብሔራዊ ቡድን ጥቅምት ወር 2006 ዓ/ም በአዲስ አበባ ስታድየም ከቀኑ 10:00 ሰዓት በሚያደርጉት ጨዋታ የአልሸባብ የሽብር ቡድን አባል የሆኑት *እነ አብዱራህማን መሀመድ* ጥቃት ለማድረስ በዝግጅት ላይ እያሉ በፀጥታ ሀይሎች በነበረው ጥብቅ ጥበቃ ምክንያት የሽብር ቡድኑ አባሎች ታጥቀውት የነበረውን ፈንጂ በአዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ክ/ከተማ ቀበሌ 01 ፈንድቶ የሽብር ቡድኑ አባሎች የሞቱ መሆኑ እየታወቀ ተከሣሽ በ21/02/2006 ዓ/ም ለአሜሪካ ድምፅ ሬድዮ ጣቢያ በሰጠው መግለጫ አሸባሪዎቹ አፈነዱ የተባለው የውሸት እና የመንግሰት ድራማ ነው በማለት የገለፀ በመሆኑ በፈፀመው ሕዝቡ በመንግስት ላይ እምነት እንዳይኖረው የሚያደርግ የሀሰት ወሬዎችን ማውራት ወንጀል ተከሷል፡፡

ብርሃኑ ወ/አገኝ
የፌደራል ፊ/ጠ/ዓ/ህግ



Scanned by CamScanner

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Federal Attorney General

ቁጥር
Ref.No
ቀን
Date

<u>የሰነድ ማስረጃ ከነ መግለጫው</u>

1. ከአባ ኤባ ለመረራ ጉዲና መጋቢት 16 ቀን 2008 ዓ/ም ጨለማ ቢመስልም አሁን እዚህ እየተደረገ ያለው ተቃውሞ በወታደር ማፈን እያቃተው ይሄዳል። 03 ገፅ ከነ ትርጉሙ፣
2. ከአበበ ቢራቱ ለመረራ ጉዲና መጋቢት 04 ቀን 2008 ዓ/ም በ7:25 ለተጎዱ ሰዎች 116,200 ብር ልከናል ጥር 26 ቀን 2008 ዓ/ም መራራ ጉዲና በወቅቱ ችግር ምክንያት በችግር ላይ ያሉትን ሰዎች መርዳት የሚፈልጉ ሰዎች አሉ 06 ገጽ ከነ ትርጉሙ፣
3. ኦ.ነ.ግ በተግባር ላይ ረቡዕ ጳጉሜ 05 ቀን 2006 ዓ/ም 10 ገጽ ከነ ትርጉሙ፣
4. ከኤባ ለመረራ ጉዲና  የተላከው ሰኞ የካቲት 28 ቀን 2008 ዓ/ም ጉዳዩ አስቸኳይ መፍትሔ የሚፈልግ መልዕክት ቄሮ ቢሉሱማ ኦሮሞ /ወጣት ብሔራዊ እንቅስቃሴ ያቋቋመው መንግስት ነው 03 ገጽ ከነ ትርጉሙ፣
5. የተላከው እሁድ መጋቢት 13 ቀን 2008 ዓ/ም ጉዳዩ ኦሮሞ በጣም አመሰግናለሁ 40,500 ብር ተቀብያለሁ የሚል 03 ገጽ ከነ ትርጉሙ፣
6. ከአብይ ዳባ ለመረራ ጉዲና ሕዳር 23 ቀን 2007 ዓ.ም ለሰባት እስረኞች 6,300 ዶላር ሰበሰብኩ በማለት በኦነግ ለተጠረጠሩና ለተከሰሱ ስለሚላክ የሚገልጽ 02 ገጽ ከነ ትርጉሙ፣
7. የኦሮሞ ቀጣይ ምዕራፍ ምንም የኦሮሞ ጠላት ህልሙን ሲቦርቅ ኦነግ በራስ ፍላጎት በተቀመጡት ቢሞላም በድንጋይ ላይ እንደወደቀች ቻይና አልሆንም 04 ገጽ ከነ ትርጉሙ፣



Scanned by CamScanner

ቁጥር
Ref.No
ቀን
Date

8. ጃዋር መሀመድ ነሐሴ 17 ቀን 2007 ዓ/ም ለመሪራ ጉዲና ኦነግ ላለፉት 40 አመታት ወደፊት አንድ ስንዝር ለመራመድ ያልቻለበት ምክንያት አንተም ታውቃለህ የሚል 05 ገጽ ከነትርጉሙ፣

9. ከጃዋር መሐመድ ህዳር 24 ቀን 2006 ዓ/ም ስራችንን ለማቀናጀት ተማክረናል ስለሌሎች ፕሮጀክት ሀሳቦች ወቅታዊ መረጃ እንሰጥሀለን የሚል 07 ገጽ ከነ ትርጉሙ፣

10. *በ14/10/2008* የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ለኦነግ አባላት ብቻ የወጣ መግለጫ በ14/04/08 ዓ/ም ከተከሣሽ ኢሜይል የተገኘ 08 ገጽ ከነ ትርጉሙ፣

11. ከተከሣሽ ኢሜይል የተገኘ የተከበራችሁ በሚል ርዕስ የመጨረሻ ጥሪ ማድረግ ለጊዜው አስፈላጊ የሆነ እርምጃ መውሰድ አለበት በወሳኝ ጊዜ ወሣኝ እርምጃ መወሰድ አለበት የሚል 11 ገጽ ከነ ትርጉሙ፣

12. ቢያ ኦሮሞ ዲሴምበር 12 የመልዕክት አካል የአምቦ አካባቢ ቄሮ ያደረገውን ጥሪ ለሁሉም ኦሮሞ እንዲደርስልን፣ በ14/4/09 ከተከሣሽ ኢሜይል የተገኘ እና ሜይ 23 ቀን ለነጋሣ ደቤ 5000 ዶላር ተቀብያለሁ የሚል 05 ገጽ ከነ ትርጉሙ፣

13. ሀሙስ ሰኔ 23 ቀን 2009 ዓ/ም የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ሸኔ የሚል 03 ገጽ ከነ ትርጉሙ፣

14. ለፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ወንጀል ምርመራ ቢሮ አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ የጻፈው ለተከሣሽ በተለያየ ጊዜ በመኒግራም መላኪያ ገንዘብ ስለመላክ የሚገልጽ በ5/2/09 የተጻፈ 02 ገጽ፣

15. ለኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ጉዳዩ በፀጥታ ችግር ምክንያት በንብረት ላይ የተደረሰውን ጉዳት ስለማሳወቅ የሚል በቀን 26/5/08 ዓ/ም የተጻፈ 02 ገጽ፣



Scanned by CamScanner

16. በቀን 26/5/08 ዓ/ም ከምዕራብ ሸዋ ዞን አስተዳደር ጽ/ቤት በኢፌዴሪ ለፌዴራል ፖሊስ ወንጀል ምርመራ ዘርፍ ዳይሬክቶሬት በተከሰተው ሁከትና ብጥብጥ ብር 17,352,482/ አስራ ሰባት ሚሊዮን ሦስት መቶ አምሳ ሁለት ሺ አራት መቶ ሰማንያ ሁለት ብር/ በላይ በንብረት ላይ የደረሰ ጉዳት በዓመፅ እና ሁከት ምክንያት በፀጥታ አስከባሪዎች ቀላል እና ከባድ ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑን የሚገልፅ 06 ገጽ፣
17. ለፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ወንጀል ምርመራ ዘርፍ ለታክቲክ ምርመራ ዳይሬክቶሬት ጉዳዩ በተከሰተው የሁከት እና ብጥብጥ በፀረ-ሠላም ኃይሎች ስለወደመው ንብረት ማሣወቅ የሚል በ25/5/08 የተጻፈ 02 ገጽ፣
18. በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የኦሮሚያ ፖሊስ ኮሚሽን በኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ወንጀል ምርመራ ቢሮ በቀን በ17/05/09 ዓ/ም በተጻፈ በኦሮሚያ ክልል በሚገኙ ዞኖች በመንግስት እና በግል ንብረቶች ላይ የወደሙትን ንብረቶች የሚገልፅ 02 ገጽ
19. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት 4ኛ ወንጀል ችሎት በመ/ቁጥር 148675 በእነ መሀመድ አብዱራህማን የአልሸባብ የሽብር ቡድን ተከሣሾች የሰጠው የጥፋተኝነት ውሣኔ *በወ/መሀ/ሥ/ሥ/ቁ 145* መሰረት የሚቀርብ ስለ 4ኛ ^ከሳ^ የሚያስረዳ፡፡
20. *1ኛተከሣሽ* ህገ-መንግስቱን እና ህገ-መንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለማስወገድ ሲያደርግ የነበረውን እንቅስቃሴ የሚገልጽ ከብሔራዊ የመረጃ እና ደህንነት አገልግሎት በቁጥር ደመ42/45/09 በቀን 14/06/09 የተጻፈ *63 ገጽ*



Scanned by CamScanner

ቁጥር
Ref.No
ቀን
Date

21. *2ኛ ተከሣሽ* ህገ-መንግስቱን እና ህገ-መንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለማስወገድ ሲያደርግ የነበረውን እንቅስቃሴ የሚገልጽ ከብሔራዊ የመረጃ እና ደህንነት አገልግሎት በቁጥር ደመ42/48/09 በቀን 14/06/09 የተጻፈ *15 ገጽ*

22. *1ኛ፣2ኛ፣3ኛ ተከሣሾች ከ4ኛ እና ከ5ኛ ተከሣሾች* ከሆኑት ለኢሣት ቴሌቪዥን እና ለኦሮሞ ሚዲያ ኔትወርክ ህገ-መንግስቱን እና ህገ-መንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለማስወገድ ሲያደርጉት የነበረውን እንቅስቃሴ የሚገልጽ ከብሔራዊ የመረጃ እና ደህንነት አገልግሎት በቁጥር ደመ42/46/09 በቀን 14/06/09 የተጻፈ *63 ገጽ*

23. ከጀዋር መሀመድ ለመረራ ጉዲና እሁድ ጥር 17 ቀን 2007 ዓ/ም በ5፡03 ፒ.ኤም በኦ.ኤም.ኤን ምን ተፈፀመ ? የሚል መልዕክት 02 ገጽ ከነ ትርጉሙ፣

24. 1ኛ ተከሣሽ በፌዴራል ፖሊስ ወንጀል ምርመራ ቢሮ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 27/2 መሠረት የሰጠው የእምነት ቃል *06 ገፅ*፣

25. ከጀዋር መሐመድ ለመረራ ጉዲና ግንቦት 17 ቀን 2007 ዓ/ም በጣም ጥሩ ሥራ ሠርታችኋል ያም እንደ ዘመቻ ስለሆነ ሕዝቡ በአመራሩ እና በአስተባባሪዎች ክብር ይሰማዋል የሚል 04 ገጽ ከነ ትርጉሙ፣

26. ለኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ ወንጀል ምርመራ ዘርፍ ታክቲክ ወንጀል ምርመራ ዳይሬክቶሬት በ16/05/08 ዓ/ም፣በ9/05/08 ዓ/ም፣በ26/5/08 ዓ/ም በ05/05/08 ዓ/ም በ21/04/08 ዓ/ም በተለያየ ጊዜ ከኦሮሚያ ክልል በሚገኝ የመንግስት መ/ቤቶች በሁከት እና ብጥብጥ ንብረት ስለወደመ ንብረት የተላከ ማስረጃ *29 ገጽ*

27. የኢትዮጵያ ብሮድካስቲግ ኮርፖሬሽን ለኢትዮጵያ ፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን በቀን 20/042009 ዓ/ም በተፃፈ ደብዳቤ *2ኛ እ 3ኛ* ተከሳሾች በኦሮሚያ ክልል እና በአንዳንድ አካባቢዎች



Scanned by CamScanner

ሲያደርጉት የነበረውን ህገ-መንግስቱን እና ህገ-መንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለማስወገድ ሲያደርጉ የነበረውን እንቅስቃሴ የሚገልጽ 01 ገፅ፣

28. የኦሮሚያ ተቃውሞ እና የወደፊት የኦሮሞ ሕዝብ የነጻነት ትግል በሚል በ2008 ዓ/ም በ1ኛ ተከሣሽ የቀረበ ***50 ገጽ*** ከነ ትርጉሙ:-

***በውስጡ የያዛቸው የማስረጃ ይዘት:-***

- በልማት ስም እየቀለበሰው የሚገኘው ይህንን መሬት ለአራሹ የሚለው መፈክር ወደ መሬት ለኢንቨስተሩ እየተባለ ነው።
- ኦነግ ያለበት የውትድርና ድክመት ከፍተኛ ቢሆንም የትግራይ ነጻ አውጪ ግንባር ጦርን ተቋቁሞ የኦሮሞ ብሔርተኝነት መንፈስ ሆኗል ገጽ [6]
- ኦነግ አጥፍቻለሁ ብሎ ሲናገር ምን ያህል ጊዜ እንደሆነ ለመቁጠር ቢያስቸግርም በሚቀጥለው ቀን ደግሞ ተነስቶ ከዚህ ድርጊት ጀርባ ያለው ኦነግ ነው ሲል እና ብዙ የኦሮሞ ወጣቶችን እንደ አሸባሪ ሲቆጥር የተለመደ ጉዳይ ሆኗል።
- በ2007 ዓ/ም የኦሮሞ ተቃውሞ ተደርጎ 78 ሰዎች ሞተዋል ለአሁኑ ተቃውሞ መቀስቀስ ምክንያት ሆኖ በስፋትም ስለሆነ ለመንግስት አስደንጋጭ ሆኗል።
- የኦሮሞ ፌደራሊስት ኮንግረስ በአሁኑ ተቋውሞ ውስጥ ያለውን አስተዋጽኦ በቅስቀሳ ስም ሚሊዮኖችን ያንቀሳቀሰ ስለመሆኑ ገፅ [9-10]
- ኦሮሞዎች አሁን ሁለት ፖለቲካ ሀይሎች አሏቸው እነዚህም በኦሮሞ ውስጥ የሚኖሩ ኦነግና ኦፌኮ ናቸው።



Scanned by CamScanner

- ለዲያስፖራ ድጋፍ ምስጋና ይሁንና ኦ.ኤም.ኤን ጨምሮ ኦፌኮ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ወጣቶችን በማንቀሳቀስ ኦሮሚያን አዳርሷል። ገፅ 14
- ለሁሉም ተግባራዊ ዓላማ ሲባል በሀገር ቤት ያለው ወጣት እንደ ጀዋር ያሉትን ሰዎች በአስተዳደሩ ላይ ባለው ተቃውሞ እንደ ኮማንደር ይቆጥሩታል በአማራ ወጣት ውስጥ ተመሣሣይ ነገር የለም።

## 5. ገላጭ ማስረጃ

- በሁሉም ተከሳሾች ላይ በቀረበው ክስ በተለያዩ ጊዜ ህገ-መንግስቱን እና ህገ-መንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለማስወገድ ሲያደርጉ የነበረውን እንቅስቃሴ የሚገልጽ፣የሁከት እና የብጥብጥ ጥሪ ሲያተላልፉ የነበረ ስለመሆኑ የሚያሳይ የድምፅ ከምስል የቪድዮ፣የኦዲዮ እንዲሁም የደረሰውን የንብረት ጉዳት የሚሳይ ፎቶ ግራፍ ብዛት 10 ሲዲዎች በችሎት የሚቀርብ ነው ።

## 6. ኢግዚቢት

- ሳምሰንግ ጋላክሲ በፌዴራል ፖሊስ ወንጀል ምርመራ ቢሮ በኢግዚቢት መዝገብ ቁጥር *160/09* የተመዘገበ ብዛት አንድ

**<u>መግለጫ</u>**

**በፀረ- ሽብርተኝነት አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀፅ 32/1 መሰረት ለምስክሮች ደህንነት ሲባል ለተከሳሾች በሚደርሳቸው ክስ ማመልከቻ ላይ ያልተገለፀ መሆኑን እንገልፃለን።**



Scanned by CamScanner